**HELLENIC REPUBLIC**
Ministry of Migration Policy

Asylum Service

**አለምአቀፍ የድጋፍ ጥበቃ ማጠየቅ ለሚገባቸውና ለጥገኝነት ጠያቀዎች መብታቸውን በተመለከተ ጥያቄና መልሶች።**

**1) ግሪክ አገር ጥገኝነት ጠያቂዎች እነዚህን የመሳሰሉ መብቶች አላቸው።**

፩) አለምአቀፍ ጥገኝነት ከጠየቃችሁ ቦሃላ አገሪቷ ወስጥ በሕጋዊ መልኩ እንድትንቀሳቀሱ የሚያስችል ካርድ ይሰጣችዋል።

፪) ነፃ የመድሃኒትና የሕክምና እንክብካቤ ይሰጣችዋል።

፫) ልጆቻችሁ ትምህርት መማር ይችላሉ።

፬) ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ገደብ መሠረት ማጠለያ የማጠየቅ መብት አላችሁ።

፭) ገድብ ያለውየ ማስራት መብት አላችሁ።

**2) የማጠለያ መብትን በተመለከተ።**

ጥገኝነት ጠያቂዎች መንግስት ባወጣውአንቀፅ 220/2007 መሠረት ማጠለያ የማጠየቅ መብት አላቸው። የሚመለከተውክፍል የሥራ ሚኒስተር ነው። የጥገኝነት አገልግሎት ቢሮ የጥገኝነት ጠያቂዎች የማጠለያ ማመልከቻ የሥራ ሚኒስተር ወስጥ ለሚከለለውለመንግስት ማህበራዊ የእርዳታ አካል ፣ የሚያስተላልፈው የሚገባውክፍል ነው።

ጥገኝነት ጠያቂዎች መብቱ ቢኖራቸወም ፣ በአሁኑ ሰዓት 1000 የሚሆን የመቀበያ ቦታ ብቻ ስላለ የሚቀርቡት ማመልከቻዎች በበቂ መልኩ ሊስተናገዱ አይችሉም። የዩሮፓውያን አንድነት (ዩሮፓዊያን ዩንየን) ባወጣውሕግ መሠረት ተቀባይነት ያገኙ የፖለቲካ ጥገኞች እና የድጋፍ ጥበቃ ለሚገባቸውየ ማጠለያ ጥያቄ መብት የላቸወም።

**3) መንግስት ሥራ ሊያገኝልን ይችላል?**

ጥገኝነት ጠያቂዎችና አለምአቀፍ ጥበቃ የሚገባቸውየ መሥራት መብት ቢኖራቸወም፥ መንግስት ለግሪክ ዜጎችምየ ሥራ ቦታ ማግኘት እንደማይችለው ሥራ ሊያገኝላችሁ አይችልም።

**4) ማለትም ግሪክ አገር የአለምአቀፍ ጥበቃ (የፖለቲካ ጥገኝነት ምሆን የድጋፍ ጥበቃ) ከተሰጠን ቦሃላ ምን አይነት መብቶች ይኖሩናል?**

፩) ነፃ ክፍያ የሚያስፈልገውመታደስ የሚቻልና የሦስት ወር የግዜ ገደብ ያለውየ መኖርያ ፍቃድ ይሰጣችዋል። ይህ የመኖርያ ፍቃድ የሚሰጣችሁ የአዎንታዊ ወሳኔ ከተሰጣችሁ ቦሃላ ነው። እስከዛ ድረስ የአለምአቀፍ ጥበቃ ስትጠይቁ የተሰጣችሁ ካርድ ላይ 'የመኖርያ ፍቃዳችሁ በእንጥልጥል' ላይ መሆኑን የሚያሳይ ማህተም ይሰፍርበታል።

፪) 85 የማያዣ ገንዘብ ከከፈላችሁና ማመልከቻ ካቀረባችሁ ቦሃላ የጉዞ ሰነድ ይሰጣችዋል። የፖለቲካ ጥገኝነት ሳይሆን የድጋፍ ጥበቃ ከተሰጣችሁ ቦሃላ ፖስፖርት ካላችሁ ወይም ከሚመለከተውየ አገራችሁ ባለሥልጣን ማውጣት ከቻላችሁ የጉዞ ሰነድ ማውጣት አይገባባቹም። በፓስፖርታቹ መጓዝ ትችላላቹ።

፫) የማስራት መብት ይኖራችዋል።

፬) የሆስፒታል እንክብካቤ ይኖራችዋል።

፫) ሆኖም የሚታይና የታወቀ አካለ ስንኩልነት ላላቸው ድጎማ ከማስጠት በቀር መንግስት ማጠለያ፣ ሥራም ሆነ ድጎማ ሊያቀርብላችሁ አይችልም።

**5) የአለም አቀፍ ጥበቃ (የፖለቲካ ጥገኝነትም ሆነ ድጋፋዊ ጥበቃ) ወሳኔ ተቀባይነት ካገኘን በሃላ የመኖርያ ፍቃድና የጉዞ ሰነድ ለመወሰድ ምን አይነት ሂደት መከተል ይገባል።**

አለም አቀፍ ጥበቃ ወሳኔ ከአገልግሎታችን ከወሰዳችሁ በሃላ ወደሚቀከተው የግሪክ ፖሊስ ጣቢያ (አቴንስ አሎዳፖን የመንገዱ ስምና ቁጥር ፔትሩራሊ 24) ሄዳችሁ የመኖርያ ፍቃዳቹ እንዲወጣ አስፈላጊ የሆኑ ወረቀቶች ማቅረብ አለባችሁ ። የግሪክ ፖሊስ ጣቢያ (አሎዳፖን) አስፈላጊ የሆኑ ወረቀቶችን ካቀረባችሁ ከ1-1,5 ወር በሃላ የጥገኝነት አገልግሎት ቢሮ መታችሁ የመኖርያ ፍቃዳችሁን መወሰድ አለባችሁ። እንዲሁም የጉዞ ሰነድ እየንዲሰጣችሁ ማመልከቻ ማስገባት ትችላላችሁ።የጉዞ ሰነድ እንዲሰጣችሁ ማመልከቻ ለማስገባት የመኖርያ ፍቃዳችሁ እንኪወጣ ማጠበቁ አስፈላጊ አይደለም። ሁለቱም ሂደቶች በአንድ ወቅት ሊፈፀሙ ይችላሉ።

**6) ለአቅመ አዳም የደረስን ትምህርት መማር እንችላለን? ግሪከኛ ቋንቋ የት መማር እንችላለን?**

የሚያስፈልጉ ነገሮችን በማሟላት የትምህርት መበት አላችሁ።

አንዳንድ ግዜ መንግሥት የግሪከኛ ቋንቋ እድል ያቀርባል። እሱን በተማለከተ የጥገኝነት አገልግሎት ቢሮ በማስታወቂያ ያሳወቃችዋል፥ እንዲሁም በዚህ ጉዳይ ተሳትፎ ካላቸው ማህበራችሁ፥ አጥቢያችሁ እንዲሁም ደግሞ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች በሚያወጡት ማስታወቂያ መረጃ ልታገኙ ትችላላችሁ።

**7) ወደተቀሩት የዩሮፕ አገር መጓዝ እንችላለን?**

በዱብሊን 3 ስምምነት መሠረት አንድ ጥገኝነት ጠያቂ ወደ ሌላ የዩሮፕ አገር በሕጋዊ መንገድ መጓዝ የሚችለው የቤተሰብ መጣመር ሁኔታ ካለ ብቻ ነው። ጥገኝነት ጠያቂው የተረጋገጠ ከባድ የጤና ችግር ደርሶበት ግዴታ ወደ ውጭ አገር በአስቸኳይ መዛወር ያለበት ካልሆነ በስተቀር ወደ ተቀረው ዩሮፕ አገር መጓዝ አይችልም።

የፖለቲካ ጥገኝነት ወይም የድጋፍ ጥበቃ ከተሰጣችሁ የጉዞ ሰነድ እንዲሰጣችሁ ማመልከቻ ማስገባት አለባችሁ። የጉዞ ሰነድ ተዘጋችቶ እስኪጨርስ ድረስ ከ1 እስከ 2 ወር ግዜ ሊወስድ ይችላል። በሚሰጣችሁ የጉዞ ሰነድ ሌላ የዩሮፕ አገር መጓዝ ትችላላችሁ ፥ እዛ መኖር ግን አትችሉም። በ6ወር ወስጥ ለ3 ወር ያህል መቀመጥ ትችላላችሁ ፥ 3ወሩ ካለቀ በሃላ ግን አገሩን ለቃችሁ መውጣት አለባችሁ። ሌላ የዩሮፕ አገር ለመኖር የምትሄዱበት የዩሮፕ አገር ለውጭ ዜጎች (ለሦስተኛ አገር ዜጎች) የሚጠይቀወን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት አለባችሁ ።

**8) አለም አቀፋዊ ጥበቃ የሚባው (የፖለቲካ ጥገኝነትም ሆነ የድጋፍ ጥበቃ) በጉዞ ሰነዱ ዩሮፕ ያልሆኑ አገር መጓዝ ይችላል?**

ይችላል ግን መጎብኘት ከሚፈልግው አገር ኤምባሲ ወይም ቆንስላ የመግቢያ ፍቃድ(Visa) ማጠየቅ አለበት። ለበለጠ መረጃ መጓዝ ወደምትፈልጉበት አገር ኤምባሲ ወይም ቆንስል ሄዳችሁ ማጠየቅ አለባችሁ።

**9) በዱብሊን 3 ስምምነት መሠረት ከማን ጋር ነው መጣመር የምንችለው?**

ተከታይ የሌላቸው ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ከቤተሰባቸው፥ ከአጎት ካክስቶቻቸው እናም ከአያቶቻቸው ጋር መጣመር ይችላሉ። እንዲሁም

ባለትዳሮች እርስ በርሳቸው።

ቤተሰቦች፥ ለአቅመ አዳም ካልደረሱ ልጆቻችቸው ጋር ።

ለአቅመ አዳም የደረሱ (ማለትም ለአቅመ አዳም የደረሱ እህትና ወንድሞች እናም ቤተሰቦች፥ ለአቅመ አዳም ከደረሱ ልጆቻቸው ጋር) በተለየ ሁኔታ ሊጣመሩ ይችላሉ። ለምሳሌ አንድ አዛውንት ከባድ የጤና ችግር ካለበትና የዘመዱም እንክብካቤ የሚያስፈልገው ከሆነ ሊጣመሩ ይችላሉ።

**10) ለዱብሊን አፈፃፀም ምን አይነት ሰነዶች ይዘን መቅረብ አለብን?**

በሌላ የዩሮፕ አገር የሚገኘው የቤተሰባችሁ አባል የሆነ ውአለም አቀፍ ጥበቃ የሚገባው ወይም ጥገኝነት ጠያቂ (የፖለቲካ ጥገኝነት ወይም የድጋፍ ጥበቃ) መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ ይዛችሁ መቅረብ አለባችሁ። ዝምድናችሁን የሚያረጋግጥ ማንኛውም አይነት ሰነድ ካላችሁ ይዛችሁ መቅረቡ ሚልካም ነው።

**11) የፖለቲካ ጥገኝነት ከተሰጠን ቦሃላ ቤተሰቦቻችንን ዩሮፕ ካልሆነ አገር እንዴት ወደ እዚህ አገር ማምጣት እንችላለን?**

የፖለቲካ ጥገኝነት የሚገባቸው፣ ትወልድ አገራቸው ከሚገኙ የቤተሰብ አባሎቻቸው ጋር፥ ማለትም ከባለቤታቸው፥ ለአቅመ አዳም ካልደረሱ ልጆቻቸው ጋር የመጣመር መብት አላቸው። ይህንንም በተመለከተ ጥገኝነት አገልግሎት ቢሮ ማመልከቻ ማስገባት ይኖርባችዋል። ይህ ሂደት ቢሮክራሲ ያለበትና ረጅም ግዜ የሚወስድ በመሆኑ በተጨማሪም ደግሞ የውጭ ጉዳይ ሚኒስተር የመሳሉ ሌሎች የመንግስት መስሪያ ቤቶችም ስለሚሳተፉ፥ ስንት የግዜ ገደብ እንደሚወስድ ሊወሰን አይችልም።

**12) የቤተሰብ አባሎቻችንን ግራክ አገር ለማምጣት የምንኖርበት ቤትና ስራ መኖር አለብን?**

የፖለቲካ ጥገኝነት ካገኛችሁበት ቀን ጀምሮ እስከ ሦስት ወር ባለው ግዜ ወስጥ የቤተሰብ መጣመር ማመልከቻ ካስገባችሁ ይሄን ጥያቄ ማሟላት አይጠበቅባችሁም።

**13) ቤተሰቦቻችንን ግሪክ አገር ለማምጣት ምን አይነት ሰነድ ያስፈልጋል? ምን አይነት የአፈፃፀም ቅድመ ሂደትስ ይከተላል?**

፩) ወደዚህ የሚመጣው ሰው ከስደተኛው ጋር ያለውን ዝምድና በቅርብ ግዜ የወጣ የቤተሰቡን ሁኔታ የሚገልጽ ወረቀት ወይም ሌላ በግሪክኛ የተተረጎመና ከሚመለከተው የግሪክ ባለሥልጣን የተረጋገጠ ሰነድ።

፪) ትክክለኛ የቤተሰብ አባሎች ወይም የአባሉ የጉዞ ሰነድ ግልባጭ።

፫) የጥገኝነት ጥያቄን የሚቀበልና የሚመረምረው የሚመለከተው ባለስልጣን ስደተኛው ከላይ የተጠቀሱትን ሰነዶች ማቅረብ ካልቻለ ሌሎች ተረጋግጠው የቀረቡ ማስረጃዎችን ጥቅም ላይ ያውላል። ይኑ ዚህን ያልቀረቡ ሰነዶችን ሚኑ በሚኑ መሠረት በማድረግ የጥያቄውን ውሳኔ ወድቅ ሊያደርግ አይችልም።

፬) ማመልከቻው ከጥገኝነት አገልግሎት ቢሮ ተቀባይነት ካገኘ ቦሃላ ዘመዳችሁ ወደ ግሪክ አገር እንዲጓዝ የግሪክ አገር ቆንስላ የመግቢያ ፍቃድ(Visa) መስጠት አለበት።

ቆንስሉ ወይም ኤምባሲው የመግቢያ ፍቃድ(Visa) ለመስጠት የሚጠይቃቸው ሰነዶች፡

፩) ፓስፖርት ወይም ሌላ የጉዞ ሰነድ ከግሪክ አገር የተረጋገጠ፣ የግዜ ገደቡም መግቢያ ፍቃዱ (Visa) ከሚያልቅበት ቀን የሦስት ወር ብልጫ ያለው መሆን አለበት።

፪) ከኢምግሬሽን ቢሮ ጥገኝነት ጠያቂውን ከወንጀል ነፃ መሆኑን የሚገልፅ ወረቀት። ይግባኝ የሌለው ማንኛውም አይነት የቅጣት ወሳኔ ካለ፣ እንዲሁም የጥገኝነት ጠያቂው ወንጀል ለአገሪቱ ደህንነት አደጋ አስከታይ አለመሆኑን ለማረጋገጥ የተለየ ምክኒያታዊ መገለጫ ይጠየቃል። የወንጀሉ ክብደትና የሕግን የመጣስ ፀባይ ሁኔታዎችም ይመዘናሉ።

፫) አለምአቀፍ የጤና ድርጅት ለሕብረተሰቡ ጤና ጎጂነው ብሎ ከሚያካትታቸው በሽታዎች ነፃ መሆኑን የሚያረጋግጥ ከመንግሥት ወይም ከግል ሀኪም ቤት ወረቀት። እንዲሁም የሕብረተሰቡን ጤና በተመለከተ እርምጃ ከሚያስፈልጋቸው ተላላፊ ወይም የተባይ መንስዔ በሽታዎች።

**14) በሚሰጠን የመኖርያ ፍቃድ ዩሮፕ አገር መጓዝ እንችላለን?**

የጉዞ ሰነድ ስለሚያስፈልጋችሁ በመኖርያ ፍቃዳችሁ ብቻ መጓዝ አትችሉም።

**15) የጉዞ ሰነድ ከማስጠቱ በፊት በከባድና በአስቸኳይ ምክኒያት ከግሪክ አገር ሌላ ውጭአገር መጓዝ እንችላለል?**

አትችሉም። ግን የተረጋገጡ አስቸኳይ ምክኒያቶች ካሉ ምናልባት የጉዞ ሰነዱ በቶሎ እንዲሰጣችሁ ሊፋጠን ይችላል።

**16) ተቀባይነት ያገኘና የጉዞ ሰነድ እንዲሰጠው ማመልከቻ ያስገባ ማመልከቻው እስኪወጣ ድረስ ምን ያህል ግዜ ይወስዳል?**

የጉዞ ሰነድ ማመልከቻ ምልስ እስኪወጣ ከ1 እስከ 1ው ከግማሽ ገደማ ይወስዳል።

**17) የግሪክ ዜግነት ለመውሰድ ምን ያስፈልጋል?**

አስፈላጊው ገደብ የግሪክ ዜግነት አንቀፅ ላይ ሰፍሮ ይታያል። በአጭሩ እናንተ ከታች የተጠቀሱትን ሁኔታዎች ማሟላት አለባችሁ።

፩) እድሜያችሁ ከ18 ዓመት በላይ የሆነ ፣ ለአቅመአዳም የደረሳችሁ መሆን አለባችሁ።

፪) አንቀፅ 5 ላይ በሰፈረው የግሪክ ዜግነትን በተመለከተ ለየት ባሉ ጽኑ ወንጀሎች የተወነጀላችሁ መሆን የለባችሁም።

፫) የፖለቲካ ጥገኛና የድጋፍ ጥበቃ ተቀባይነት ያገኛችሁ ወይም እነ ዚህን ጥበቃ ያገኙ የቤተሰብ አባል የሆናችሁ መሆን አለባችሁ። እንዲሁም ደግሞ የመኖርያ ፍቅድ መኖር አለባችሁ።

፬) በቂ የግሪክኛ ቋንቋ ማወቅ አለባችሁ።

፭) የግሪክ ዜግነትን በተመለከተ አንቀፅ 5A ላይ እንደሚገልጸው የግሪክ ዜግነት ጠያቂ በአገሪቷ የምጣኔ ሃብት፣ ማህበራዊ እናም በፖለቲካ ኑሮ ዙሪያ የተሳትፎ አስተዋጽኦ ማበርከት አለበችሁ።

**18) የመኖርያ ፍቃድና የጉዞ ሰነድ ለስንት ግዜ ያገለግላሉ?**

የመኖርያ ፍቃድ የሦስት ዓመት የግዜ ገደብ አለው።

የሚታደሰውም የእድሳት ማመልከቻ ካስገባችሁ ቦሃላ ነው።

የጉዞ ሰነድ ደግሞ ለአምስት ዓመት ያገለግላል።

**19) ኑሮዋቸው ዩሮፒያን ዩንየን ያልሆነ፣ ጥለናቸውም ከመሄዳችን በፊት አብረውን የሚኖሩ ከእኛም እርዳታና እንክብካቤ የሚጠብቁ ከነበሩና፥ ሌላ የሚንከባከባቸው ሰው ከሌላቸው ቤተሰብ ወይም እህትና ወንድሞቻችን ጋር መጣመር እንችላለን?**

ለአቅመአዳም የደረሰ የፖለቲካ ጥገኛ ከቤተሰቡ ጋር በተለየ ሚሊኩ መጣመር ይችላል።

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት የቤተሰብ መጣመርን በተመለከተ በተጨማሪ ማቅረብ ያለባችሁ ሰንዶች፡

፭) ለአገሩ ዜጋ ሠራተኞችም በተመሳሳይ ሜኬኩ እንደሚያስፈልገው ስደተኛውም ለራሱም ሆነ ለሚያስተዳድራቸው ቤተሰብ የተሟላ የጤና ዋስትና መኖሩን የሚያሳይ መንግስታዊ የደህንነት ዋስትና ሰነድ

፮) የግብር ክፍያ ወረቀት ወይም ገቢው አገሪቷ ከምትሰጠው ድጋፍ የሚመጭ አለመሆኑንና የግል አመታዊ ገቢው ለራሱም ሆነ ለቤተሰቡ በቂ፥ ጽኑና የሚያቋርጥ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማንኛውም አይነት መንግስታዊ ሰነድ። ይህ ገቢ ምጭቅ ካልሆነ ሠራተኛ አመታዊ አበል ያነሰ መሆን የለበትም። የባለቤቱ 20% ፣ የአባትና እናት እንዲሁም የልጆች 15% የበዛ መሆን አለበት። እንዲሁም

፯) ስደተኛው ከመንግስት ምጣኔ ሃብት አገልግሌት፣ ለራሱም ሆነ ለቤተሰቡ ግዚያዊ መኖሪያ ቤት ያለው መሆኑን የሚያሳይ የተረጋገጠ የቤት ግዢ ወይም የቤት ክራይ ወል

**20) የፖለቲካ ጥገኝነት ወይም የድጋፍ ጥበቃ እንዳይሰጠንና ከተሰጠን ቦሃላ ምልንቀማ የሚያስችሉ ወንጀሎች ምን አይነት ናቸው?**

ከታች የተዘረዘሩ ሥራዎች ከአለም አቀፍ ጥበቃ (ከፖለቲካ ጥገኝነት ወይም ከድጋፍ ጥበቃ) መታገድ ወይም መነጠቅን ያስከትላሉ፡

ከባድ ወንጀል ወይም ጥፋት፥ ቢያንስ በሦስት ዓመት እስራት የሚያስቀጣ እንዲሁም ከባድ የአካል ጉዳት ሚድረስ ወንጀልና (310 የወንጀለኛ መቅጫቁጥር)፥ ሕፃን ልጅን አስገድዶ መነጠቅ (324 ወ.መ.ቁ) ፥ ለአቅመ አዳም ያልደረሰችን በፍቃደኝነቷም ቢሆን መጥለፍ (327 ወ.መ.ቁ)፥ የሰውን ልጅ ክብር ማዋረድና መዝለፍ (337 ወ.መ.ቁ ምእራፍ 2-5)፥ ሕፃን ልጅን አታሎ መድፈር (339 ወ.መ.ቁ)፥ ሕፃን ልጅን አታሎ ፍትወተ ሥጋ መፈጸም (342 ወ.መቁ)፥ የሕፃናት ሽርመጥና ቀረፃ መፈጸም (348A ወ.መ.ቁ)፥ ሕፃናትን ለመዝለፍና ለማዋረድ መቅረብ (348A ወ.ቁ.መ)፥ ማሸርሞጥ፥ በሴተኛ አዳሪ ማጠቀም፥ ገንዘብ ከፍሎ ከሕፃናት ጋር የፍትወተ ሥጋ መፈጸም፥ ማስፈራራት (385 ወ.መ.ቁ)።

**21) በፈለግነ ውሰዓት የአለም አቀፍ ጥበቃ (የፖለቲካ ጥገኝነት ወይም የድጋፍ ጥበቃ) ጥያቄያችንን ማቋረጥ እንችላለን?**

የጥገኝነት ጥያቄችሁን በፈለጋችሁበት ግዜ ማቋረጥ ትችላላችሁ። እንዲሁም የፖለቲካ ጥገኝነት ሆነ የድጋፍ ጥበቃ ቢሰጣችሁም ጉዳዩ እንዲቋረጥ ሚድረግ ትችላላችሁ። ጉዳዩ እንዲቆም ካደረጋችሁ ቦሃላ ግን አገሩን ለቃችሁ መውጣት አለባችሁ።